ከፍታ የወጣቶች ኃ/የተወሰነ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር አሰራር ስርዓት

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

ነሀሴ 2015

አዲስ አበባ

1. መግቢያ 2
2. ትርጓሜ 2
3. የህብረትስራማህበሩየብድርአላማ 3
4. የኅብረት ስራ ማህበሩየብድርዓይነቶችእናየአገልግሎትአፈጻጸም፣ 4
4.1. የፍጆታብድር-- 4
4.1.1. ለፍጆታብድርየሚቀርብየዋስትናአይነት-- 4
4.1.2. የማበደሪያወለድመጠንናአወሳሰን-- 5
4.2. የንግድብድር-- 5
4.2.1. የንግድብድርዋስትናአይነት-- 6
4.3. ለቤትግዥ፣መስሪያናማደሻየሚሰጥብድር-- 6
4.4. የተሽከርካሪግዥብድር-- 7
5. ዋስትናስለማንሳት 8
6. የብድርማመልከቻአቀራረብ 9
7. የብድርአፈቃቀድ 10
8. ብድርየሚከለከልባቸውምክንያቶች 11
9. የብድርውል 11
10. የተፈቀደየብድርገንዘብንስለመልቀቅ 12
11. የብድርክትትልናቁጥጥር 12
12. የብድርአመላለስሥርዓት 12
13. የብድርመክፈያጊዜንስለማራዘም 13
14. በወቅቱስላልተሰበሰበብድር 14
15. ዕዳንስለማቻቻል 14
16. ዕዳንለማስመለስክስስለመመስረት፣ 15
17. ዕዳንከመዝገብስለመሰረዝ 15
18. ከአባላትውጭየሚሰጥብድር 16
19. የመመሪያውትክክለኛነትስለማረጋገጥ 16

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከፋታ የወጣቶች ኀ/የተ/መሰ/ህ/ስ/ማ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd. Liab

ጥር /2016**አዲስ አበባ**

አጭርርዕስ

ይህ መመሪያ የከፍታ ወጣቶች ገንዘብ ቁጠባና ብድር መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር የብድር አስተዳደር መመሪያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 01/ 2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

1. መግቢያ

ከፍታ ወጣቶች የገንዘብ ቁጠባና ብድርኃ.የተ. መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚሰጠውን የብድር አገልግሎት ፍትሃዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና ከዋናው ቢሮ እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በአግባቡተግባራዊማድረግአለበት።በመሆኑም ኅብረት ሥራማህበሩ የብድር አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ብድር አገልግሎቱን በአግባቡ መምራት የሚያስችል የብድር መመሪያ እና ደንብ ማዘጋጀት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው።

የብድር መመሪያው ለብድር አገልግሎት ፈላጊው አባላትም ሆነ ለአገልግሎት ሰጪው ኅብረት ስራ ማህበር ግልጽና ለአፈፃፀም አመች መሆን ስላለበት ህብረት ስራ ማህበሩ የሚሰጣቸው የብድር ይነቶች፣የብድር ገንዘብጣሪያ፣የማበደሪያ ወለድ አወሳሰን የብድር ዋስትና፣የብድር ማመልከቻ አቀራረብ፣የብድር አፈቃቀድና ገንዘብ የመልቀቅ ሥርዓት፣ብድር የሚከለከልባቸው ምክንያቶች፣የብድር ውሉ መያዝ ያለበት ነጥቦች፣የብድርክትትልና ቁጥጥር ፣የብድር አመላለስ ሥርዓት፣የብድር መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም፣ ግዴታውን ባልተወጣ ተበዳሪ ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ እና የመሳሰሉትን ያካተተነው።

በመሆኑም ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የብድር አገልግሎቱን በአግባቡ መምራት የሚያስችል ይህንን የብድር አስተዳደር መመሪያ አዘጋጅቷል።

2. ትርጓሜ

ኅብረት ስራ ማህበር ማለት በኅብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት የተደራጀ እና በሚመለከተው አካል የተመዘገበ የከፍታ ወጣቶች የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኃላፊነቱ የተወሰነ መሰረታ ኅብረት ስራ ማኅበር ማለት ነው።

ጥር /2016**አዲስ አበባ**

አባል ማለት በኅብረት ስራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 በተደራጀ እና በተመዘገበ በከፍታ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ሃላፊነቱ የተወሰነ መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበር ውስጥ የአባልነት መመዘኛዎችን አሟልቶ የተመዘገበ ግለሰብ ማለት ነው።

ብድር ማለት አንድ የኅብረት ስራ ማህበራችን አባል የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመው ከኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር የውል ስምምነት መሰረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተወስዶ ከነወለዱ ተመላሽ የሚደረግ የገንዘብ ልውውጥ ማለት ነው።

አዋጅ ማለት የኅብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ነው

ያልተመለሰ ብድር ማለት ብድሩ ተሰጥቶ እንዲመለስ በውል ከተወሰነበት ጊዜ ውስጥ ከ30 ቀን በላይ ሳይመለስ ያለፈው ብድር ማለት ነው።

የማይመለስ ብድር ማለት ብድሩ ተሰጥቶ እንዲመለስ በውል ከተወሰነበት ጊዜ ውስጥ ከ360 ቀን ወይም አንድ አመት በላይ ሳይመለስ ያለፈው ብድር ማለት ነው።

የቡድን ብድር ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰብ አባላት በፍላጎታቸዉ በተናጠል ተበድረዉ በመካከላቸዉ በሚኖረው ስምምነት በአንድ የንግድ ስራ እቅድ በጋራ እንዲሰሩ የሚሰጥ የብድር አይነት ነው።

የማይመለስ ብድር መጠባበቂያ ማለት ኅብረት ስራ ማህበሩ ከሰጣቸው ብድር ውስጥ ያልተመለሰ እና የማይመለስ ብድር ማካካሻ የሚሆን ከጠቅላው ገቢ ቀንሶ የሚያስቀምጠው እና በወጭ የሚመዘግበው ማለት ነው።

3. የህብረትስራማህበሩየብድርአላማ

- ለአባላት የተለያዩ አይነቶች የብድር አገልግሎት በመስጠት ንግዳቸውን የሚያንቀሳቅሱበት እና የሚያስፋፉበት እንዲሁም ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያሳኩበት የገንዘብ አቅም በመፍጠር የአባላትን ገቢ አስተማማኝ እንዲሆን እና የተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲደርሱ ማድረግ።
- የአባላት የብድር አጠቃቀም እና የገንዘብ አያያዝ ልምድ እና ባህል ማዳበር
- የስራ ዕድል መፍጠር እና የስራ አጥ ቁጥርን በመቀነስ የሃገር ኢኮኖሚ ግንባታ የበኩላችን አስተዋፅዎ ማበርከት ነው።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

4. የኅብርት ስራ ማህበሩ የብድርዓይነቶችእናየአገልግሎትአፈጻጸም፣

4.1. የፍጆታብድር

የፍጆታብድርማለት፤-ለትምህርት፤

ለህክምናለቤትእቃማሟያእናለሌሎችማህበራዊአገልግሎቶችየሚውልሲሆንይህብድርየሚወሰነውማንኛው ምተበዳሪየሚያቀርበውንየብድርመጠየቂያመሠረትበማድረግበኅ/ስ/ማህበሩናበተበዳሪውአባልመካከልበ ሚደረግየብድርውልስምምነትሆኖየመጨረሻየብድርመመለሻጊዜ**2(ሁለት)አመት**ያልበለጠእናከፍተኛየብ ድርመጠን**150,000 /አንድመቶሃምሳሽብር /**ድረስመሆንአለበት።

ተበዳሪውብድሩንለማግኘትከዚህበታችያሉትንመስፈርቶችማሟላትአለበት፡-

- ለተከታታይ 3(ሦስት ወራት) ያህል የቆጠበ መሆን አለበት
- ተበዳሪው የብድሩን 25% አስቀድሞ ያለማቃረጥ በተከታታይ የቆጠበ መሆን አለበት
- የቀበሌ መታውቂያ፤ የጋበቻ/ያገባ ያላገባ) ማስረጃ ማቅረብ የሚችል/የምትችል

4.1.1. ለፍጆታብድርየሚቀርብየዋስትናአይነት

- የተበዳሪው ወይም የአባሉ ዕጣና ቁጠባ፤
- የሌሎች አባላት የዕጣና ቁጠባ፤
- አባል ያልሆኑ (አዋቂዎችና የህጻናት) ቁጠባ፤
- ከመንግስት ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚቀርብ የዋስትና ደብዳቤ

  ይህንን ደብዳቤ በዋስትናነት ለመያዝ ዋሱ ከሚሰራበትመስሪያ ቤትየደመወዙመጠን፤ ቋሚሰራተኛመሆኑንናጡረታለመውጣትየቀረውጊዜ፤

  ዋሱመስራቤቱንቢለቁበቅድሚያየሚያሳዉቁመሆኑን እና የስራ ግብር ከፋይ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤ዋሱ ማህበሩ ጽ/ቤት በአካል ቀርቦመፈረምአለበት/ባት

- የንበረት ዋስትና፤-

  ተበዳሪው የራሱን ወይም የሌላ ሰው ከእዳና እገዳ ነጻ የሆነ (የቤት ካርታና ፕላን የሚያቀርብ፤ የመኪና ሊብሬ የሚያቀርብ እንዲሁም ያልተከፈለ ቦንድ የሚያቀርብ/ከሆነ ብድሩን መውሰድ ይችላል።

- የቦንድ እና አክሲዮን ድርሻ ዋስት

ጥር /2016**አዲስ አበባ**

አክሲዮን የተገዛበት ድርጅት ባንክ፣ ማይክሮ ፋይናንስ እና ኢንሹራንስ ፣ ሪል እስቴት፣ ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት መሆን አለበት።የአክሲዮን ሰርተፊኬት ማስረጃው የተገዛበት ቀን የሰርተፊኬት ቁጥር የአክሲዮን ብዛት ያንዱ ዋጋ እና ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ ያለበት የአክሲዮን ማህበሩ ባለስልጣን ፊርማ እና ማህተም ያለበት መሆን አለበት። ተበዳሪው ከአክሲዮን ማህበሩ ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ በዕዳ ያልተያዘ ለመሆኑ እና በማህበራችን ስም ታግዶ ማስረጃ መቅረብ አለበት።

4.1.2. የማበደሪያወለድመጠንናአወሳሰን

- ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበሩ አባል ብድሩንበሚበደርበትወቅትበሚደረገውስምምነትመሠረትበወርበቀሪዕዳላይ እኩል የሆነ የአከፋፈል ስርዓት ወለድይከፍላል።
- የኅብረት ስራ ማህበሩየብድርወለድመጠንለውጥየሚያደርግከሆነተበዳሪዎቹበለውጡመሠረት ኅብረትስራማህበሩ በውስጥ ማስታወቂያ ለ10 ተከታታይ ቀናት ካሳወቀ አባሉ የተደረገውን ማስተካከያ ተፈፃሚነት ይቀበላሉ።
- የብድር ክፍያ በወቅቱ ከነወለዱ በውሉ መሠረት ካልተከፈለ ባልተከፈለው የወለድ መጠን ያህል /እኩል የሆነተጨማሪ በቅጣት ይከፍላል።
- የብድር ወለድ መጠን<u>ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች</u> **<u>12 ፐርሰንት</u>** በዓመት የሚታሰብ ሲሆን ለሌሎች አባል ተበዳሪዎች ደግሞ **<u>12.25 ፐርሰንት</u>** በዓመት የሚታሰብ ይሆናል።

4.2. የንግድብድር

አንድአባልበግሉምይሁንበቡድን(ከ2-7የሆኑተበዳሪዎችአንድላይበመሆን) ንግድለመጀመርወይምንግድለማስፋፋትለንግድአገልግሎትየሚሰጥብድርሲሆንብድሩየሚወሰነውማንኛ ውምተበዳሪየሚያቀርበውንየብድርመጠየቂያመሠረትበማድረግበኅብረትስራማህበሩናበተበዳሪውመካከል በሚደረገውየውልስምምነትይሆናል።

የዚህብድርየመጨረሻየብድርመመለሻጊዜ5(አምስት)ዓመትድረስይሆናል።የብድርመጠኑበግል ለሚበደሩ አባላት እስከ 500,000.00/አምስትመቶ ሺህ ብር/ በቡድን ተደራጅተው ለሚበደሩት እስክ 800,000.00/ስምንትመቶሺብር/ድረስይሆናል።

ብድሩንለመውሰድከዚህበታችያሉትመስፈርቶችመሟላትአለባቸው።

- ተበዳሪው/ የቡድን አባልቱ **ለተከታታይ** 3 ወር ሳያቋርጥ/ጡ የቆጠበ መሆን አለበት፤
- ተበዳሪው/ተበዳሪዎቹ የብድሩን 25 ፐርሰንት አስቀድሞ መቆጠብ አለበት/አለባቸዉ፤
- ተበዳሪው/ተበዳሪዎቹ ለሚበደረው/ለሚበደሩት ብድር በቂ ዋስትና ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት ፤

ጥር /2016**<u>አዲስ አበባ</u>**

- ተበዳሪው/ተበዳሪዎቹ የቀበሌ መታወቂያ ያለው/ያላቸዉ እና ያገባ እና ያላገባ ማስረጃ የሚያቀርብ/የሚያቀርቡ መሆን አለበት፤
- የማበደሪያ ወለድ መጠን ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች **12 ፐርሰንት** በዓመት የሚታሰብ ሲሆን ለሌሎች አባል ተበዳሪዎች እና ለቡድን ተበዳሪዎች ደግሞ **12.25 ፐርሰንት** በዓመት የሚታሰብ ይሆናል።
- የቢዝነስ ፕላን/እቅድ/ ማቅረብ ይኖርበታል።

4.2.1. የንግድብድርዋስትናአይነት

- የአባሉ የዕጣና የቁጠባ ዋስትና
- የሌሎች አባላት የዕጣና ቁጠባ ዋስትና
- አባል ያልሆኑ (የህጻናትና አዋቂዎች) ዋስትና
- ከመንግስት ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚቀርብ የዋስትና ደብዳቤ በዋስትናነት ለመያዝ ዋሱ ከሚሰራበትመስሪያ ቤትየደመወዙመጠን ቋሚሰራተኛ መሆኑንና ጡረታ ለመውጣት የቀረው ጊዜ፤ዋሱመስራቤቱንቢለቁበቅድሚያየሚያሳዉቁመሆኑን እና የስራ ግብር ከፋይ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤ዋሱ ማህበሩ ጽ/ቤት በአካል ቀርበመፈረምአለበት/ባት።
- የንበረት ዋስት፤- ተበዳሪው የራሱን ወይም የሌላ ሰው ከእዳና እገዳ ነጽ የሆነ (የቤት ካርታና ፕላን የሚያቀርብ፤የመኪና ሊብሬ የሚያቀርብ እንዲሁም ያልተከፈለ በንድ የሚያቀርብ/ከሆነ ብድሩን መውሰድ ይችላል።
- የበንድ እና አክሲዮን ድርሻ ዋስት አክሲዮን የተገዛበት ድርጅት ባንክ፣ ማይክሮ ፋይናንስ እና ኢንሹራንስ ፣ ሪል እስቴት፣ ሆስፒታል፣ትምህርት ቤት መሆን አለበት። የአክሲዮን ሰርተፊኬት ማስረጃው የተገዛበት ቀን የሰርተፊኬት ቁጥር የአክሲዮን ብዛት ያንዱ ዋጋ እና ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ ያለበት የአክሲዮን ማህበሩ ባለስልጣን ፊርማ እና ማህተም ያለበት መሆን አለበት። ተበዳሪው ከአክሲዮን ማህበሩ ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ በዕዳ ያልተያዘለመሆኑ እና በማህበራችን ስም ታግዶ ማስረጃ መቅረብ አለበት

4.3. ለቤት መስሪያና ማደሻ የሚሰጥ ብድር

አዲስ የመኖሪ ቤት እና የንግድ ቤት ለመገንበት የሚሰጥ ብድርና ነባር የመኖሪ ቤት እና የንግድ ቤት ለመጠገን የሚሰጥ ብድር ሲሆን፤

ብድሩየሚወሰነውማንኛውምተበዳሪየሚያቀርበውንየብድርመጠየቂያመሠረትበማድረግበኅብረትስራማህ በሩናበተበዳሪውመካከልበሚደረገውየውልስምምነትሆኖ የመጨረሻ የብድር መመለሻ ጊዜ **5/አምስት/** አመት ሆኖ ከፍተኛ የብድር መጠን 400,000/አራት መቶ ሺ ብር/ ድረስ ነው።ብድሩን ለመውሰድ

- አንድአባልቢያንስስድስት ወራት እና ከዚያ በላይ ያለማቋረጥ በተከታታይ የቆጠበመሆንአለበት፣
- የብድሩን 30 በመቶ አስቀድሞ በተከታታይ የቆጠበ መሆን አለበት፣
- የቀበሌ መታወቂያ ያለው እና ያገባና ያላገባ ማስረጃ የሚያቀርብ መሆን አለበት
- የማበደሪያ ወለድ መጠን የማበደሪያ ወለድ መጠን ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች 13. **25 ፐርሰንት** በዓመት የሚታሰብ ሲሆን ለሌሎች አባል ተበዳሪዎች ደግሞ 13.50 ፐርሰንት በአመት የሚከፍል መሆን አለበት፤

4.4. የተሽከርካሪ ግዥ ብድር

4.4.1ይህየብድርአይነትለንግድአገልግሎትየሚውሉባለሦስትዕግርየሰውናየጭነትባጃጅእንዲሁምበለ 4 እግርባጃጅናዳማስተሽከርካሪንያካትታል፤**አንድአባልበግሉምይሁንበቡድን (ከ2-7አባላት) የተሽከርካሪብድርመጠየቅይችላሉ**ብድሩየሚወሰነውማንኛውምተበዳሪየሚያቀርበውንየብድርመጠየቂ ያመሠረትበማድረግበኅብረት ስራ

ማህበሩናበተበዳሪውመካከልበሚደረገውየውልስምምነትሆኖየመጨረሻየብድርመመለሻጊዜ**5**አመትያልበለ ጠሆኖየብድርጣራለባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪ እስከ **700,000** ብርመሆንአለበት።ብድሩንለማግኘት

- አንድአባልየተሽከርካሪብድርአገልግሎትጥያቄለማቅረብናለማግኘትለባለ ሶስት ተሽከርካሪ ቢያንስ4ወርእናከዚያበላይያለማቋረጥበማህበሩውስጥየቆጠበመሆንአለበት፣
- የብድሩን25ፐርሰንትአስቀድሞየቆጠበመሆንአለበት፤
- የሚገዛውንተሽከርካሪሊብሬእናሌሎችመረጃዎችለብድሩዋስትናነትማስያዝየሚችልመሆንአለበት፤
- ከታወቀየኢንሹራንስድርጅትመሉዋስትናየተገባለትመሆኑንየሚገልጽበቂመረጃማቅረብአለበት፤
- ከሚኖርበትቀበሌመታወቂያእናየጋብቻመረጃማቅረብየሚችልመሆንአለበት፤
- የሚገዛውተሽከርካሪእድሜከተሰራበትጊዜጀምሮከ 10 ዓመትያልበለጠመሆንአለበት፤
- የማበደሪያ ወለድ መጠን ለሶስት እግር ተሽከርካሪ ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች 12.5 እና ለሌሎች 13ፐርሰንትበዓመት የሚከፍል መሆን አለበት፣

ጥር /2016**አዲስ አበባ**

4.4.2 ለባለ አራት እግር ተሽከርካሪ

ይህየብድርአይነትለንግድአገልግሎትየሚውሉባለአራትዕግርየሰውናየጭነትተሽከርካሪንያካትታል፤

አንድአባልበግሉምይሁንበቡድን (ከ2-7አባላት)

የተሽከርካሪብድርመጠየቅይችላሉብድሩየሚወሰነውማንኛውምተበዳሪየሚያቀርበውንየብድርመጠየቂ ያመሠረትበማድረግበኅብረት ስራ

ማህበሩናበተበዳሪውመካከልበሚደረገውየውልስምምነትሆኖየመጨረሻየብድርመመለሻጊዜ**5**አመትያልበለ ጠሆኖየብድርጣራእስከ **1,500,000.00 ብር**መሆን አለበት። ብድሩንለማግኘት

- አንድአባልየተሽከርካሪብድርአገልግሎትጥያቄለማቅረብናለማግኘትለባለ አራት እግር ተሽከርካሪ **6** ወር እናከዚያበላይያለማቋረጥበማህበሩውስጥየቆጠበመሆንአለበት፣
- የብድሩን**30**ፐርሰንትአስቀድሞየቆጠበመሆንአለበት፤
- የሚገዛውንተሽከርካሪሊብሬእናሌሎችመረጃዎችለብድሩዋስትናነትማስያዝየሚችልመሆንአለበት፤
- ከታወቀየኢንሹራንስድርጅትመሉዋስትናየተገባለትመሆኑንየሚገልጽበቂመረጃማቅረብአለበት፤
- ከሚኖርበትቀበሌመታወቂያእናየጋብቻመረጃማቅረብየሚችልመሆንአለበት፤
- የሚገዛውተሽከርካሪእድሜከተሰራበትጊዜጀምሮከ 10 ዓመትያልበለጠመሆንአለበት፤
- የማበደሪያ ወለድ መጠን ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች 13.25 እና ለሌሎች 13.5**ፐርሰንት**በዓመት የሚከፍል መሆን አለበት፤

5. ዋስትናስለማንሳት

- ተበዳሪውያለበትንዕዳእየከፈለቀሪውዕዳውከቁጠባናዕጣመጠንጋርተመጣጣኝከሆነብድሩተከፍሎሳ ያልቅበዋስትናየተያዘውየዋሱቁጠባወይምንብረትእየታየእንደአስፈላጊነቱሊለቀቅይችላል፣ ሆኖምየቁጠባውመጠንከቀሪብድርመጠንበላይመሆንአለበት፤

- የተበዳሪውዋስትናየቁጠባእናየዕጣመጠንለሌሎችተበዳሪዎችየብድርዋስትናከሆነእናተበዳሪውበተን ቀሳቃሽወይምበቋሚንብረትዋስትናተበዳሪከሆነእናቀሪዕዳውበቁጠባውእናዕጣመጠንተመጣጣኝከ ሁነያስያዘውቋሚእናተንቀሳቃሽንብረትዕዳውተከፍሎእስኪጠናቀቅድረስዋስትናውይነሳል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን Ethiopian Cooperative Commission መዝገብ ቤት Archive አዲስ አበባ

ጥር /2016

- ዋስትናመቀየርበሚያስፈልግበትጊዜተመጣጣኝዋስትና /ተያዥ/ በኅብረትስራማህበሩገማችኮሚቴወይምማህበሩበሚወክለውባለሙያየዋጋግምቱታይቶዋጋውተ መጣጣኝመሆኑሲረጋገጥእናበአዲሱ/ተተኪውዋስትናውልሲያዝብቻነው። ውሉንእንደገናለመዋዋልወጪየሚጠይቅከሆነወጪውበተበዳሪውየሚሸፈንይሆናል።

6. የብድርማመልከቻአቀራረብ

- ህብረት ስራ ማህበሩ ለአባላት የብድር መስፈርት የሚያሟሉ እና ብድር ለመበደር እቅድ ያላቸውን አባላት ለመመዝገብ በሚያወጣው የጊዜ ሰለዳ መሰረት መመዝገብ አለባቸው፤

6 1 በቅርንጫፍ ቢሮዎች የሚሰጥ ብድር የጊዜ ሰሌዳ

- ከ1_5 ባሉ የስራ ቀናቶች የብድር ማመልከቻ መቀበል
- ከ6_10 ባሉ የስራ ቀናቶች የብድር ኮሚቴ አስተያየት ይሰጣል
- ከ11_15 ባሉ የስራ ቀናቶች የዶክመንት ማሟላት ስራ ይሰራል
- ከ16_20 ባሉ የስራ ቀናቶች የቅርንጫፍ ኮሚቴ ሰብሰቢና ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ብጋራ ብድሩን ያጸድቃሉ
- ከ21_30 ባሉ የስራ ቀናት የብድር ስርጭት ማድረግ

6 2 በዋና ቢሮ የሚሰጥ ብድር የጊዜ ሰሌዳ

- ከ16_20 ባሉ የስራ ቀናቶች የብድር ኮሚቴ ዉሳኔን ማመልከቻ መቀበል
- ከ21_25 ባሉ የስራ ቀናቶች የብድር ኮሚቴ አስተያየትን ይገመግማል
- ከ26 እስከ 10 ባሉ የስራ ቀናት የብድር ስርጭት ማድረግ ይኖርባቸዋል።
- በብድር መጠየቂያ ቀን ተበዳሪ አባላት በቅርንጫፍ ቢሮዎች ብቻ በአካል በመቅረብ ወይም በተዘጋጀው ሲስተም on line በመጠቀም ጥያቄ ሊያቀርቡ ወይም ሊመዘገቡ ይችላሉ፤
- አባላት ብድር ለመበደር ምዝገባ ለማካሄድ ሲመጡ የአባልነት የቁጠባ ደብተራቸውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤
- ብድርፈላጊዎች ኅብረትስራማህበሩባዘጋጀውየብድርማመልከቻቅጽሞልተው ለኅብረት ስራ ማህበሩያቀርባሉ፣

- ኅብረትስራማህበሩ የቀረቡለትን የብድር ማመልከቻዎች እንደ አቀራረባቸው ቅደም ተከተል መሠረት ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ያስተናግዳል፣
- ከብድር ማመልከቻውጋርበአባሪወይምበደጋፊማስረጃነትየሚቀርቡሰነዶች፤-
  - የቁጠባናየዕጣገንዘብመጠን
  - ለተበዳሪውዋስየሆኑአባላትቁጠባናየዕጣገንዘብመጠን፣
  - ለዋስትናየቀረበውቋሚንብረት በኅብረትስራማህበሩ የስራ ዋና መ/ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባለበት አከባቢ ሆኖ፣ ዝርዝር ህጋዊ ሰነዶች እናየባለሙያ አስተያየትና የኢንሹራንስግምት መኖር አለበት፣
  - የጋብቻሰርተፊኬትየተበዳሪውናየዋሱ፤የታደሰየቀበሌመታወቂያ፤
  - የሥራዕቅድወይምብድሩየተፈለገበትአላማ

7. የብድርአፈቃቀድ

ኅብረትስራማህበሩማንኛውንምየቀረበለትንየብድርጥያቄበሙሉወይምበከፊልለመፍቀድወይምለመከልከ ልዝርዝርየብቃትግምገማለማካሄድየሚከተሉትንነጥቦችማጤንይኖርበታል።

- የተበዳሪው የገንዘብ አጠቃቀም ልምድ /ችሎታ/፣
- የአባሉ የቁጠባ አቆጣጠብ ሁኔታ ቅድመ ቁጠባው መጠንና ተከታታይ መሆኑን፤
- ያቀረበው ዋስትና ተመጣጣኝ መሆኑን፣
- የአመልካቹ ግዴታ የመወጣት ታሪክ፣ ቀደም ሲል የተሰጠውን ብድር ዓይነትና ለተባለው ጉዳይ የማዋል ሁኔታ፣
- ተበዳሪው ኅብረትስራማህበሩ ጋር ያለው የአገልግሎት ተጠቃሚነት ወይም የጠበቀ ግንኙነት፣
- ማህበሩ ለብድር አገልግሎት ሊያውል የሚችለውን የገንዘብ አቅምና የብድር አመልካቾች በወቅቱብድሩንየመክፈልችሎታ፣ወዘተ
- የብድር ማመልከቻው በኅብረትስራማህበሩ ብድር ባለሞያ አማካኝነት አስፈላጊው መረጃዎች መሟላታቸው ተረጋግጦ ለቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ እና ለቅርንጫፍ ኮሚቴ ተወካይ ሰብሳቢከብድር ኮሚቴ አስተያየት ጋር ያቀርባል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

- ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጁ እና የቅርንጫፍ ኮሚቴ ተወካይ ሰብሳቢአስፈላጊ ነው ብለው ካመኑ ስለ ብድር ማመልከቻውና ሌሎች በአባሪነት የቀረቡ መረጃዎችንና ሌሎች ጉዳዮች በይበልጥ ግልጽ እንዲሆንአቸው ቃለ-መጠይቅ ማድረግ ይችላሉ
- ለቅርንጫፍ ስራ አስኪያጁ እና ለቅርንጫፍ ኮሚቴ ተወካይ ሰብሳቢ የቀረበውን የብድር ጥያቄ ካልተቀበሉት ያልተቀበሉበትን ምክንያት በዝርዝር በመግለጽ ለአመልካቹ ያሳውቃሉ፣
- ብድር ጠያቂው ብድር የተከለከለበት ምክንያት ከደንቡና ከብድር መመሪያው ውጪ የተፈፀመ ነው ብሎ ካመነ ለዋና ቢሮ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፤
- ዋናዉ ቢሮ የቀረበለትን ይግባኝ ከሚመለከታቸው አካላቶች ጋር በመሆን መፍትሄ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
- ከብድር መጠየቂያ የጊዜ ሰሌዳ ውጭ የሚመጡ አስቸኳይ የብድር ጥያቄዎች ለጤናና ለአልታሰበ አደጋዎች እንደሁኔታው እየታየ ሊስተናገድ ይችላል፤
- የብድር ጣሪያ እና አፈቃቀድ በተመለከተ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት እስከ 700,000.00 ድረስ በዋናዉ መስሪያቤት ደግሞ ከ700,000.00 ብር በላይ ያለዉን ይፈቅዳል።

8. ብድርየሚከለከልባቸውምክንያቶች

ኅብረትስራማህበሩከዚህበታችበተጠቀሱትምክንያቶችብድርሊከለክልይችላል።

- በዕቅድናበዓላማላይያልተመሠረተየብድርጥያቄሲቀርብ፣
- ያለበቂምክንያትያለበትንየብድርክፍያአቋርጦበግፊትእንዲከፍልየተደረገተበዳሪ፣
- ከሌሎችአበዳሪአካላትተበድሮግዴታውንያልተወጣ፣
- የመክፈልአቅሙና፣
  ተበዳሪውያለበትማኅበራዊናኢኮኖሚያዊሁኔታብድርለመመለስእንቅፋትይሆናልተብሎሲታመን፣
- ዋስትና ማቅረብ የማይችል ከሆነ፣-
- ለተበዳሪ ዋስ ሆኖ ተበዳሪው ያለበትን ብድር እንዲከፍል ሀለፊነቱን ያልተወጣ አባል ከሆነ፤
- በሌሎች መሰል ምክንያቶች፣

9. የብድርውል

- ኅብረትስራማህበሩለሚሰጠውብድርአግባብነትያለውበሕግፊትተቀባይነትያለውውልይይዛል፣
- ተበዳሪው እና ዋሱ በአካል በኅብረትስራማህበሩ ጽ/ቤት በአካል በመገኘት ታዛቢዎች /እማኞች/ ባሉበት ይዋዋላሉ፡-

- ስልጣን ያለው እና ውሉ በተፈፀመበት ቀን በአካል ተገኝተው ይፈርማሉ።
- አንድ አባል ብድሩን ሲወስድ የብድሩን **1% (አንድ ፐርሰንት)** አነስተኛ የብድር መድህን ሽፋን አገልግሎት ይቆረጥበታል፤
- የብድር አገልግሎት ክፍያ ማህበሩ ብድሩን ሲሰጥ ለብድር አገልግሎት ክፍያ 1% (አንድ በመቶ) ከተበዳሪው ላይ ይቆርጣል፤
- ውሉ በበቂ ቅጅ ተዘጋጅቶ ለአበዳሪው፣ ለተበዳሪውና ለዋሱ /ሶች/ አንድ የውል ቅጅ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፤

10. የተፈቀደየብድርገንዘብንስለመልቀቅ

- የብድርገንዘብከመለቀቁበፊትየብድርገንዘብለመልቀቅአስፈላጊየሆኑነገሮች /ውልመዋዋሉንና፣ ዋስትናመያዙን/ መረጋገጥአለበት፣
- ለተበዳሪው የተፈቀደውን የብድር ገንዘብ በአንድ ጊዜ ወይም በ2 ጊዜ ቀናንሶ መልቀቅ ይቻላል። በከፊል የሚለቀቅ ከሆነ ቀሪውን የብድር ገንዘብ ለመልቀቅ ቀድሞ የተለቀቀው ገንዘብ አጠቃቀም ከታየ በኋላ ይሆናል፣
- ብድሩ ተከፋፍሎ የሚሰጥ ከሆነ ብድር መመለስ የሚጀምረው የመጀመሪያ ብድር ከወሰደበት በወሩ ጀምሮ ይሆናል፤
- ማህበሩለተበዳሪውየሚሰጠውንየብድርገንዘብበቼክ ወይም በቀጥታ በአካውንቱ ይከፍላል፣

11. የብድርክትትልናቁጥጥር

- ኅብረትስራማህበሩ የተሰጠው ብድር ለተባለው ተግባር በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣
- የተሰጠው ብድር ከኅብረትስራማህበሩ ዕውቅና ወይም ፈቃድ ውጭ ለተባለው ተግባር ሥራ ላይ አለመዋሉከተረጋገጠየመመለሻጊዜውሣይደርስእንዲመለስይደረጋል፣

12. የብድርአመላለስሥርዓት

- የብድር አመላለስ ሥርዓቱ የሚወሰነው ተበዳሪው ብድሩን የሚያውልበት ተግባራትን መሠረት በማድረግበኅብረትስራማህበሩ እና በተበዳሪውመካከልበሚደረግ የብድር ውል ስምምነትሲሆንከብድርዘመንመብለጥየለበትም

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

ጥር /2016 **አዲስ አበባ**

- በብድር ውሉ በተወሰነው የጊዜ ገደብ መሠረት በየወሩ ተከፍሎ የሚመለስ የክፍያ ሰሌዳ መሰረት ዋና ተመላሽ፤ ወለድ፤ መደበኛ ቁጠባ አብሮ መከፈል አለበት ሆኖም ከመክፈያው ጊዜ በፊት ማጠናቀቅ ይቻላል
- በየወሩ እየመጡ መክፈል ለማይችሉ ዋናውን ከነወለዱ የሚፈልጉትን ወር ያህል አስቀድመው መክፈል ይችላሉ
- በወር ከአንድ ጊዜ በላይ የብድር ተመላሽ የሚከፍሉ አባላት ተጨማሪውን ክፍያ ያለወለድ መክፈል ይችላሉ፤
- ወሩን አሳልፎ የከፈለ ተበዳሪ በቀሪው እዳ ላይ ላልተከፈሉባቸው ለያንዳንዱ ወራት በብድር ውሉ መሰረት የተቀመጠውን ያልተከፈለ ወለድ ያህልቅጣትይከፍላል፤
- አንድ ተበዳሪ ብድሩን ከነ ወለዱ ማህበሩ በከፈተው አካውንት ቁጥር በአቅራቢያው በሚገኝ ባንክ በመሄድ መክፈል ይችላል ወይም በ on line በቀጥታ መክፈል ይችላል ወይም በማህበሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአካል በመገኘት መክፈል ይችላል፡፡

13. የብድርመክፈያጊዜንስለማራዘም

- ተበዳሪዎችየወሰዱትንየብድርገንዘብበውሉመሠረትየመክፈልግዴታአለባቸው፡፡ ይሁንእንጂተበዳሪውከአቅምበላይበሆነበአሳማኝችግርምክንያት ማለትም ጦርነት፤የተፈጥሮ አደጋ፤ወረርሽኝ የሞት አደጋ ብድሩንበውሉመሠረትመክፈልየማይችልበትጊዜሲከሰትየብድርመክፈያጊዜሊራዘምይችላል፡፡
- የብድርመክፈያጊዜንለማራዘምየሚከተሉትንሁኔታዎችመሟላትይኖርባቸዋል፡፡
- ተበዳሪው የብድር ክፍያ ጊዜ ይራዘምልኝ ጥያቄን ከአሣማኝ ምክንያት ጋር በጽሁፍ ሲያቀርብ፣
- የማራዘም ጥያቄው ተግባራዊ የሚሆነው የቅርንጫፍ ቢሮ ሰብሰቢውና ቅርንጫፍ ስራስኪያጅ ሲቀበሉትና ስምምነቱን በጽሁፍ ሲያሳውቁ፣
- የተበዳሪው ዋሶች በብድር መክፈያ ጊዜው አምነው ከተቀበሉና በፊርማቸው ሲያረጋግጡ ወይም ሌላ ዋስትና ሲቀርቡና አስፈላጊው ውል ሲያዝ፣ የብድር መክፍያ ጊዜው እስከ ሦስት ወር ሊራዘም ይችላል፣
- የብድር መክፈያ ጊዜን ለማራዘም ለሚከናወኑ ተግባራትና ለሚወጡ ወጪዎች መሸፈኛ ኅብረትስራማህበሩበጥናት ላይ የተመሠረተየአገልግሎትክፍያ ተበዳሪውን ሊያስከፍልይችላል፡፡

- በአንድ የብድር ውል ዘመን ለአንድ ተበዳሪ የሚደረግ የብድር ማራዘም ጥያቄ ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው

14. በወቅቱስላልተሰበሰበብድር

- ኅብረትስራማህበሩ በወቅቱ ገቢ ያልሆነን ብድር ከሚመለከታቸው አካላት/ተበዳሪ መሰብሰብ እንዲችል ክፍያ ያዘገየውን ተበዳሪ ሥም፣ ያቀረባቸውን ዋሶች ወይም ያስያዘውን ዋስትና ያልተሰበሰበውን የብድር መጠን፣ ብድሩ ገቢ ሣይሆን የቆየበት ጊዜ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን በማጥናትና በማቅረብ በማነጋገርና ገንዘቡን በወቅቱ ለማስመለስ ይቻል ዘንድ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርባቸዋል።
- የብድር ክፍያ በተቋረጠ በ60 ቀናት ውስጥ የተቋረጠበትን ምክንያት ማጣራትና ተበዳሪዎችንና ዋሶችን በማነጋገር ክፍያው ወዲያውኑ የሚቀጥልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- በተደረገው ውይይት ክፍያውን እስከ 30 ቀናት ድረስ ካልቀጠለ/ካልጀመረ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪውና ለዋስ/ሶች ይሰጣል፣
- በተሰጠው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መሠረት ተገቢውን ክፍያ በ30 ቀናት ውስጥ ካልፈፀመ ሥርዓቱን ተከትሎየዕዳማካካስሥራይፈፀማል፣

15. ዕዳንስለማቻቻል

- ተበዳሪው በተለያዩ ምክንያት በገባው ውል መሠረት በወቅቱ ብድሩን መክፈል ባይችል ኅ/ስ/ማህበሩ የተበዳሪውን መደበኛ ቁጠባ፣ ዕጣና ሌሎችንም ድርሻዎች ተበዳሪውን መጠየቅ ሳያስፈልግ ለዕዳ ማካካሻ ማዋል ይቻላል። ይህም ሆኖ ዕዳው ሊካካስ ካልቻለ የዋሶች ዕጣ እና ቁጠባ እንዲሁም የስያዙት ንብረት ለዕዳ ማካካሻ በፍ/ቤት ውሳኔ እንዲውል ይደረጋል፣
- የተበዳሪውንና የዋሱንቁጠባናእጣንእዳማካካሻስለማዋል
  - ተበዳሪው ያለበት ዋና ተመላሽ፤ ወለድ፤ ቅጣት እንዲሁም ያለው ቁጠባና ዕጣ ከዋሱ ጭምር በኅብረትስራማህበሩ የቁጠባ እና ብድር ባለሙያ እንዲሁም ሂሳብ ሰራተኛ ተረጋግጦ ለኅ/ስ/ማህበሩ ቁጠባ እና ብድር ኃላፊ እና ህግ ክፍል ቀርቦ ተበዳሪዎች ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆናቸው ሲረጋገጥ ለስራ አስኪያጁ በፅሁፍ ሲቀርብ በሂሳብ ክፍል ኃላፊ አማካኝነት እዳው እንዲቻቻል ይደረጋል።

- ስራ አኪያጁየዕዳማቻቻልእንዲካሄድለኅብረትስራማህበሩሂሳብሰራተኛውሳኔያሳልፋል፤

16. ዕዳንለማስመለስክስስለመመስረት፣

- ኅብረትስራማህበሩለአባላትያበድረውን የብድር ገንዘብበኅብረትስራማህበሩ እና በተበዳሪዎች እንዲሁም በዋስትና ውል መሰረት እና በተሰጠውማስጠንቀቂያመሰረትሊከፍሉፈቃደኛላልሆኑ ተበዳሪዎችአግባብላለውፍርድ ቤትበማቅረብ ከሰ ማስመለስ ይችላል።
- ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ተበዳሪ በተሠጠው ጊዜ ውስጥ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ የኅ/ስ/ማህበሩ የህግ ክፍል በኩል አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦ ብድሩ እንዲመለስ ይደረጋል።
- ኅ/ስ/ማህበሩ አግባብላለውፍርድቤትበማቅረብከሰማስመለስይችላል። ለዚህምየሚያስፈልጉወጪዎች ለጊዜው በኅብረትስራማህበሩየሚሸፈንሆኖኅብረትስራማህበሩብድሩን ለማስመለስ ያወጣውን ወጪ በተከሳሽ ዕዳ ላይ ተደምሮ እንዲከፍል ይደርጋል።

17. ዕዳንከመዝገብስለመሰረዝ

- በኅብረትስራማህበሩ ለተለያዩ አገልግሎቶች ብድር ወስደው በተለያዩ ምክንያት ብድራቸውን መክፈል ያልቻሉ እና የተበዳሪዎች እና የዋሶቹ ዕጣ እና ቁጠባ ዕዳውን ማካካሻ ከተደረገ በኋላ ለብድሩ ዋስትና የተያዘ ተጨማሪ ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረት በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶ በሃራጅ በመሸጥ ዕዳው ተከፍሎ ዕዳውን መዝጋት ያልተቻለ እና በብድር ውሉ ብድር ማጠናቀቂያ ጊዜ መሰረት ዕዳው ያልተከፈለ መሆኑ በኅብረትስራማህበሩየቁጠባ እና ብድር ክፍል፣ሂሳብ ክፍል እና ህግ ክፍል ተረጋግጦ ቀርንጫፍ ለስራ አስኪያጅ፤ለዋናው መ/ቤት ስራ አስኪያጅ እና ለስራ አመራር ኮሚቴ ቀርቦ በጠቅላላ ጉባኤ ተወካዮች እንዲሰረዝ ከፀደቀ በኋላ ብድሩ ይሰረዛል።
- የተሰረዘ ብድር ተለይቶ ይመዘገባል። ሆኖም ተበዳሪው የሚከፍልበት ሁኔታ ከተገኘ እንዲከፍል ይደረጋል ።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ... The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

18. ከአባላትውጭየሚሰጥብድር

- ኅብረትስራማህበሩከተለያዩ ተቋማት በሚያደርገው የውል ስምምነት መሰረት ዋስትናውን እና ለብድር የሚውለው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ የአስተዳድሩልኝ ጥያቄ በሚያቀርበው ተቋም የሚሸፈን መሆን አለበት
- ለዚህ ብድር የሚውል ገንዘብ በሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት ከብድሩ ተጠቃሚዎች ላይ የሚገኝ ወለድ በስምምነቱ መሰረት ለኅብረትስራማህበሩ ገቢ ይሆናል
- የውል ስምምነቶች ሁል ጊዜ የኅብረትስራማህበሩ ጥቅም የሚያስከብር መሆን አለበት
- ኅብረት ስራ ማህበሩ ከተለያዩ ተቋማት የሚቀርብትን የብድር አስተዳድሩልኝ ጥያቄ የውል ስምምነት የሚፈጸመው በዋናው ጽ/ቤት በኩል ሲሆን ተፈጻሚነቱ እንደሁኔታው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በኩል ሊሆን ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive

19. የመመሪያውትክክለኛነትስለማረጋገጥ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

ጥር /2016 አዲስ አበባ

ይህ መመሪያ ያካተታቸው አንቀጾች የኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር መመሪያን አንድ በአንድ ተወያይተን ያፀደቅናቸውና በትክክል የመመሪያው አካል ስለመሆናቸው እኛ የከፍታ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበር ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በእያንዳንዱ የመመሪያው ገጽና ከዚህበታች በስማችን ፊት ለፊት ባስቀመጥነው ፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

የሰራአመራርኮማቴአባላት

ሙሉስም	የሥራድርሻ	ፊርማ
1. [illegible]	የቦርድሰብሳቢ	
2. [illegible]	ም/ቦርድሰብሳቢ	
3. [illegible]	የማህበሩፀሀፊ	
4. [illegible]	አባል	
5. [illegible]	አባል	
6. [illegible]	አባል	
7. [illegible]	አባል	
8. [illegible]	አባል	
9. [illegible]	አባል	

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic ... Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

ጥር /2016**አዲስ አበባ**